የሰበር መ/ቁ. 18307

ጥቅምት 25 ቀን 1998

ዳኞች፡ - 1. አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

2. አቶ ፍስሐ ወርቅነህ

3. ወ/ሮ ስንዱ ዓለሙ

4. ወ/ሮ ደስታ ገብሩ

5. አቶ አሰግድ ጋሻው

**አመልካች፡ - ንብ ትራንስፖርት አ.ማ**

**መልስ ሰጪ፡ - አቶ ተገኑ መሸሻ**

ለዚህ የሠበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ጉዳይ የተጀመረው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ነው፡፡

በሥር ፍ/ቤት የአሁን ተጠሪ ከሣሽ ሲሆን አመልካቹ ተከሣሽ ነበር፡፡

የተሰጠው የሥራ ክስ በድርጅቱ ውስጥ የቴክኒክ ዋና ክፍል ሀላፊ ሆኜ ስሠራ ከታህሣሥ 23/94 ዓ.ም. ጀምሮ ከሥራ ታግጄ ከቆየሁ በኂላ ሰኔ 5/95 የተፃፈ የስንብት ደብዳቤ ተሠጥቶኛል ስለዚህ



ከታገድኩበት ጊዜ አንስቶ እስከተሠናበትኩበት ጊዜ ድረስ ያለው የ17 ወር ከ15 ቀን የተጣራ ደመወዜ 23.500 (ሃያ ሦስት ሺህ አምስት መቶ ብር) ወጪና ኪሣራ ተጨምሮ ይከፈለኝ የሚል ነው፡፡

የሥር ተከሳሽ ማለትም ተጠሪው ቀርቦ የይርጋ መቃወሚያ አንስቶ በብይን ውድቅ የተደረገበት ቢሆንም ፍሬ ጉዳዩን በተመለከተ ከሣሽ ከሥራ የተሠናበተው ድርጅቱን የሚጐዳ ተግባር የፈፀመ መሆኑን በመግለጽ ሥራ ላልሠራበት ጊዜ ደመወዜ ሊከፈለው እንደማይገባ ይከፈለው ቢባል እንኳ ከ3 ወር ደመወዝ ሊበልጥ እንደማይችል በመግለጽ ተከራክሯል፡፡

ክሱ የቀረበለት ፍ/ቤትም ከሣሽ የሥራ መሪ እንደመሆኑ በፍ/ህጉ ላይ የሥራ መሪን ከሥራ ስለማገድ የተደነገገ ድንጋጌ የለም፣ በድርጅቱ የውስጥ ደንብ ስለመኖሩና በውስጥ ደንቡ መሠረት ስለማገዱ አላስረዳም በመልስ የዘረዘራቸውን ተግባራት ከሣሽ ፈጽመዋል ቢባል እንኳ ከሥራና ከደመወዝ ለማገድ በቂ ምክንያቶች አይደሉም በፍ/ሕ/ቁጥር 2574/1 ሠራተኛው አገልግሎት ባይሰጥም ይህ የሆነው በአሠሪው ምክንያት ከሆነ ደመወዝ የመክፈል ግዴታ አለበት፣ የ3 ወር

ደመወዝ ብቻ ሊከፈላቸው ይገባል የሚለው የተከሣሽ ክርክር በፍ/ሕ/ቁጥር 2574/2/ የተመለከተው የ3 ወር ደመወዝ ክፍያ የሥራ ውሉ ለተቋረጠበት እንጂ የሥራ ውሉ ለታገደበት ጊዜ የሚመለከት አይደለም በማለት ክስ የቀረበበትን ገንዘብ ተከሣሽ ለከሣሽ እንዲከፍል ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካቹ በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ቢያቀርብም በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሠረት ይግባኙ ተሠርዞበታል፡፡

አመልካቹ የሥር ፍ/ቤቶች ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ስላለበት ይታረምልኝ ሲል በ14/5/97 የተፃፈ የሰበር አቤቱታ አቅርቧል፡፡

የአቤቱታው ፍሬ ቃል ተጠሪው በ5/10/95 እና በ5/2/95 ተጽፎ የተሰጣቸው ደብዳቤ የሥራ ስንብት ሣይሆን የሥራ ልምድ የምስክር ወረቀት መሆኑን የሥር ፍ/ቤት በአግባቡ አልመረመረም፡፡

አመልካች ተጠሪን ከሥራ ለማገድ ምክንያት ያደረገው በድርጅቱ ሥራና ገንዘብ ላይ በተለያዩ ጊዜያት ጉዳት ማድረሣቸውን የሚያመለክቱ



ናቸው፡፡ ፍ/ቤቱ የፍ/ሕ/ቁጥር 2575 ስለ ሥራ ውል መቋረጥ እንጂ ስለ ሥራ ውል ማገድ የሚመለከት አይደለም ያለው ያለአግባብ ነው፣ ተጠሪው በእገዳ ላይ ለቆዩበት ጊዜ ሥራ እንዳይሠሩ የከለከላቸው ድርጅቱ ነው ተብሎ ደመወዙ ይከፈለው መባሉ ስህተት ነው ምክንያቱም የፍ/ሕ/ቁጥር 2540 ሥራ ላልተሠራባቸው ቀኖች ሠራተኛው ደመወዝ ለማግኘት መብት የለውም የሚለውን የሚቃረን ነው፡፡ የፍ/ህግ ቁጥር 2574/2/ ከ3 ወር የማይበልጥ ክፍያ እንዲከፈል የደነገገው የሥራ ውል ሲቋረጥ ብቻ ነው ተብሎ የተሰጠው ትርጉም ስህተት ነው በአጠቃላይ የሥር ፍ/ቤቶች ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ሥህተት ያለበት ስለሆነ ውሣኔዎቹ ተሽረው ወጪና ኪሣራ ተከፍሎን እንሠናበት የሚል ነው፡፡

የሰበር አቤቱታ ማመልከቻው ለተጠሪው ደርሶ ሚያዝያ 19/1997 ዓ.ም. በተፃፈ መልስ የአመልካች የሰበር አቤቱታ የሕግ ስህተት መፈፀሙን አይገልጽም፣ የ6 ወር የጊዜ ገደብ የከሣሽን የጥቅም ጥያቄ በይርጋ አያግደውም፣ ተጠሪው በጥፋት ተከስሼ አላውቅም፣ ባልተቀጣሁበት ጉዳይ ጥፋት ነው ተብሎ ለሠበር አቤቱታ መቅረቡ

ያለአግባብ ነው፣ ተጠሪ በ5/10/95 እና በ5/2/95 የተፃፈው የሥራ የምስክር ወረቀት እንጂ የሥራ ስንብት ደብዳቤ አይደለም ያሉት የፍሬ ነገር ክርክር እንጂ የህግ ስህተት መሆኑን አያመለክትም፣ አመልካች መ/ቤት ከሥራና ከደመወዝ ያለበቂ ምክንያት አግደውና አሰናብተው ስለአጉላሉኝ በደሉ ታይቶ የተሰጠው ውሣኔ የሕግ ስህተት ሳይሆን የፍሬ ነገር ክርክር ነው፣ በፍ/ሕግ ቁጥር 2540 ሥራ ላልሠራባቸው ቀኖች ደመወዝ ሊከፈለው አይገባም ለተባለው ተጠቃሹ ህግ ሠራተኛው ሥራውን በራሱ ፍላጐት ሣይሠራ ሲቀር እንጂ አሠሪው ሥራ ሲከለክለው የሚጠቀስ አይደለም፣ የፍ/ሕግ ቁጥር 2574/2/ ለኪሣራ እንጂ ውዝፍ ደመወዝን የሚመለከት አይደለም፣ ከዚህ ጉዳይ ጋርም ግንኙነት የለውም ስለሆነም ጥያቄው ከበቂ ኪሣራ ጋር ተሠርዞ እንድሠናበት በማለት ሲከራከር አመልካቹ አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልሱን አቅርቧል፡፡

በግራ ቀኙ መካከል የቀረበው ክርክር ከፍ ብሎ በዝርዝር የተመለከተው ሲሆን፣ በኛ በኩል ተጠሪው ከሥራ ታግዶ ለቆየበት ጊዜ ደመወዙ ይከፈለው መባሉ ተገቢ መሆን አለመሆኑን አግባብ ካላቸው



ሕጐች ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡ ተጠሪው በአመልካቹ ድርጅት ውስጥ የሥራ መሪ ሆኖ ሲሠራ የነበረ በመሆኑ የአመልካችና የተጠሪው የሥራ ክርክር የሚዳኘው በፍትሐብሔር ሕጉ በአንቀጽ 16 የሥራ አገልግሎትን መስጠት ስለሚመለከቱ ውሎች ከቁጥር 2512 እና ተከታታይዎቹ በተደነገጉት ሕጐች መሠረት ነው፡፡

የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የአሠሪን የሥራ ውል ስለማቋረጥ እንጂ አሠሪን ከሥራ ስለማገድ በፍ/ብሔር ሕጉ የተቀመጠ ድንጋጌ የለም ካለ በኋላ በፍ/ሕግ ቁጥር 2541/1/ መሠረት አመልካቹ ተጠሪውን ከሥራና ከደመወዝ አግዶ ለቆመባቸው ወራቶች ደመወዙን ይክፈለው ሲል ወስኗል፡፡

በመሠረቱ ከፍ/ሕግ ቁጥር 2534 ድንጋጌ በግልጽ መረዳት የሚቻለው ደመወዝ ለተሠራ ሥራ ብቻ የሚከፈል እንጂ ላልተሠራ ሥራ የሚከፈል አይደለም፡፡

የፍ/ብሔር ሕግ ቁጥር 2540 ይህንኑ የሕጉን መርህ በመከተል ሥራ ላልተሠራባቸው ጊዜያት ወይም ቀናት ሠራተኛው ደመወዝ ለማግኘት መብት የለውም በማለት ግልጽ ድንጋጌ አስፍሮ ይገኛል፡፡

ይሁንና የፍ/ሕግ ቁጥር 2541/1/ ሠራተኛው አንድም የሥራ አገልግሎት ባይሠጥም እንኳን ይኸው ሁኔታ አሠሪው የሥራ ሣይሠጠው በመቅረቡ ወይም እንዳይሠራ በመከልከሉ የተነሣ የሆነ እንደሆነ ደመወዙን ለማግኘት መብት አለው ሲል ሠራተኛው የሥራ ውሉ ባልታገደበት ወይም ባልተቋረጠበት ጊዜ ሥራ ላይ ሆኖ ነገር ግን አሠሪው ሥራ ሣይሠጠው ወይም እንዳይሠራ በከለከለው ጊዜ የሚያገለግል እንጂ ሠራተኛው ከሥራና ከደመወዝ ታግዶ የሥራ አገልግሎት ላልሠጣባቸው ጊዜያት ደመወዝ እንዲከፈለው የሚፈቅድ ድንጋጌ አይደለም፡፡

ስለሆነ የሥር ፍ/ቤቶች ውሣኔ ብቻ ብለው በተመለከቱት የፍ/ብሄር ድንጋጌዎች አተረጓጐም ረገድ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመባቸው በመሆኑ ሊሻሩ ይገባል ብለናል፡፡

**<u>ውሣኔ</u>**

የፌ/ከፍ/ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 34240 በ5/5/97 የሠጠው ውሣኔ እና የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 1119 በ1-2-97 የሠጠው ውሣኔ



በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት የተሻሩ ስለሆነ የውሣኔው ግልባጭ ለሥር ፍ/ቤቶች ይድረሳቸው መዝገቡ ተዘግቷል ለመ/ቤት ይመለስ፡፡